ሚያዚያ 2003

# የወጣቶቻችን ስደት ለማስቀረት ምን ማድረግ እንችላለን?

## ክፍል አንድ

### ከሱመ

ጥር 2003 በዚህ ድረ-ገጽ ለኢሮብ ወጣቶች ስደት ሶስቱ መሰረታዊ ምክንያቶች በሚል ርእስ የጻፍኩት ጽሁፌን ቀጥሎ በተቀመጠው ፓራግራፍ ነበር የዘጋሁት።

*"እንግዲህ እኔ የኢሮብ ወጣቶች መሰረታዊ ችግሮች ናቸው ያልኩዋቸውን ከላይ እንደተመለከታችሁት አስቀምጫለሁ። ጉዳዩ የሁላችን ጉዳይ ስለሆነ እያንዳንዱ/ዷ ያገባኛል፣ የኢሮብ ህዝብ ችግር ችግሬ ነው፣ የሚል/ትል፣ የኢሮብ ወጣቶች ዛሬ ገብተውበት ያለው አጅግ ከፍተኛ ቀውስ የሚያሳስበው/ባት ችግሩ ሙሉ በሙሉ ከቁጥጥራችን ውጭ ወጥቶ በህልውናችን ላይ ከፍተኛ አደጋ ከማስከተሉ በፊት በአንድነት ይህን ችግር ከስር መሰረቱ ለመቅረፍ ማድረግ ያለብን እናድግር። በሚቀጥለው ይህን የወጣቾቻችን ስደትና ተስፋ መቁረጥ ለማሰቀረት ምን ማድረግ አለብን በሚለው በኔ በኩል የሚታዩኝን የመፍትሄ ሃሳቦች ይጄ እቀርባለሁ* በሚል ነበር።

ዛሬ ልጽፍበት ወደ ተነሳሁበት የመፍትሄ ሃሳቦች ከመግባቴ በፊት ለምን እስከዛሬ ዝምታን እንደመረጥኩ ትንሽ ልበል። ለቆይታዬ ዋነኛው ምክንያት በመጣጥፌ አንባቢያን የሚሉት ነገር ቢኖር ትንሽ ጊዜ በመስጠት የሚሰጡዋቸውን አስተያየቶች በመጣጥፌ ውስጥ ለማጠቃለል ከመፈለግ በተጨማሪ ኑሮን ለማሸነፍ የሚደረገው ውጣ ውረድም ቁጭ ብዬ ሃሳቤን አሰባስቤ ለመጻፍ አልፈቅድ ስላለኝ ነው። ዛሬ ግን በገባሁት ቃል መሰረት የወጣቶቻችን ስደት ለመቀነስ ብሎም ለማሰቀረት በኔ በኩል መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸው ሃሳቦቼንና አስተያየቶቼን በሁለት ዓበይት ክፍሎች በመክፈል በተከታታይ ለማቅረብ ብቅ ብያለሁ።

በመጀመሪያ ለመከታተል እንዲያመች በኔ እምነት ለወጣቶቹ ስደት መሰረታዊ ምክንያቶች ናቸው፣ አስቸኳይ መፍትሄም ይሻሉ የምላቸውን ሁለቱን መሠረታዊ ነጥቦች ላስቀምጥ።

1. *ድህነት፣ በአከባቢው የተንሰራፋው የስራ እጦትና ተስፋ የሚሰጥ እንቅስቃሴ ለማየት አለመቻል፣*

2. *በስልጣን ላይ ያለው ገዢ ፓርቲ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ረገጣና ለገነዘብ ሲሉ ወጣቶችን ለስደት የሚመለምሉ ወንጀለኛ ግለሰቦች መኖር፣* ሲሆኑ አስቸኳይ ዘላቂና መሠረታዊ መፍትሄ ሊፈለግላቸው የሚገቡ ችግሮች ናቸው።

## 1.ድህነትን ለማስወገድ፣ ሥራ የማግኘት ተስፋ የሚሰጥ የልማት እንቅስቃሴ በአከባቢው ለመፍጠር  ምን ማድረግ እንችላለን?

መፍትሔ ሐሳቦችን ከመጠቀ‌ማችን በፊት አስቀድመን ችግሮቹን ለይተን ማወቅና ችግሮች መኖራቸውን መቀበል የመፍትሄው የመጀመሪያ አዎንታዊ እርምጃ መሆኑ በሁላችንም ዘንድ የጋራ መግባባት መኖር አለበት። ይህ መግባባት ሲኖር የችግሮቹን ጥልቀት፣ ስፋትና የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ በግልጽ በመወያየት የጋራ ስምምነት/ውሳኔ ላይ መድረስ ይቻላል። በዚህ መሰረትም ለውይይታችን መንደርደሪያነት እንዲረዳ በኔ በኩል የኢሮብ ህዝብ ዛሬ ያለበት የድህነትና በከአበባቢው የስራ ዕድል ሊፈጥሩ የምችሉ ተቋማት አለመኖር ለበርካታዎቹ ወጣቶቻችን መሰደድ መሰረታዊ ምክንያቶች ናቸው ብዬ አምናለሁ።

የኢሮብ ህዝብ የሚኖርበት የኢሮብ ምድርን ስመለከተው፣ መሬቱ ልክ እራቆቱን እንደወጣ ሰው እራቆቱን የቀረበት፣ ገበሬዎች መሬት አልባ የሆኑበት፣ በአካቢው ለወጣቶቹ የስራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ ተቋማት ያለመኖር ሁኔታ በግልጽ ጎልተው ከሚታዩ ችግሮች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ይህ በእንዲህ እንዳለ በአከባቢው ካለው ድርቅ መንግስትም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአከባቢው ከሚያደርጉት የልማት እንቅስቃሴ እጥረት አንጻር መሬት አልባ ለሆኑ ወጣት አርሶ አደሮች የስራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሉም።በአከባቢው የሕብረተ-ሰቡን የኑሮ ሁኔታ ሊቀይሩ የሚችሉ ልማታዊ ተቋማት አለመኖራቸው ወለል ብሎ በግልጽ የሚታይ ጉዳይ ነው። ስለሆነም በአከባቢው የሚታረስ የራሳቸው መሬት ያጡ፣ ስራ ያጡ፣ በአከባቢው የወደፊት ተስፋ ሊያሳዩዋቸው የሚችሉ ተቋማት ማየት ያልቻሉ ወጣቶች የግድ ወደ ተለያየ አቅጣጫ በጣም አደገኛ የሆነው መንገድም ሁሉ ጭምር በመውሰድ ለመሰደድ እየተገደዱ ናቸው። አንባቢያንስ ምን ትላላችሁ?

## ይህን ችግር ለመቅረፍ ምን ማድረግ ይቻላል?

የኢሮብ ወረዳ ዛሬ ደርሶበት ካለው መራቆት አስወጥተን፣ በአከባቢው ለወጣቶቹ የስራ ዕድል ፈጥረን ወጣቶቹን ከስደት ለማስቀረት የሚያስችል አቅም እኛ የኢሮብ ብሂረሰብ አባላት ለብቻችን ይኖረናል የሚል እምነት በበኩሌ የለኝም። ይህንን ችግር ከስር መሰረቱ ለመቅረፍ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ተሳትፎ የግድ ይላል። ይህ በእንዲህ እያለ በኛ በብሂረሰቡ አባላት መደረግ የሚገባቸው እስከ ዛሬ ያላደረግናቸው በርካታ ስራዎችና መውሰድ የሚገባን እርምጃዎች መኖራቸውን ግን ፈጽሞ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው። ስለሆነም መሰባሰብና ማድረግ የሚገባንን የምናደርግበት ጊዜ ገና ድሮ የነበረ ቢሆንም፣ ምንም ካለማድረግ ዘግይቶም ቢሆን አንድ ነገር ማድረግ የተሻለ መሆኑን ተቀብለን፤ አሁን በኛ በብሂረሰቡ ተወላጆች ደረጃ ይህን ችግር ለመቅረፍ ማድረግ አለብን ብዬ የማምንባቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች እንደሚከተው አቀርባለሁ።

**የሚታዩኝ የመፍትሄ ሃሳቦቼ፣**

1. ዛሬ የኢሮብ ህዝብ ከማንኛውም ጊዜ በላይ ትክክለኛ ችግሩን የሚናገርለትና የሚሟጎትለት የኔ ነው የሚለው ወገን አጥቷል ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። በተጨማሪም እንደ እኔ እምነት ዛሬ የኢሮብ ህዝብ ከምን ጊዜም በላይ የታፈነና ማንነቱም ቀስ በቀስ እየተገዘገዘ በመጥፋት ላይ ያለ ህዝብ ነው። በመሆኑም፤ ዛሬ የኢሮብ ህዝብ ከምንጊዜም በላይ ችግሩን የሚናገርለትና የሚሟገትለት ወገን ያስፈልጓል። ስለሆነም ከግል ጥቅምና ፍላጎት ወጣ ብለን ማየት የምንችል ልጆቹ ከምንጊዜም በላይ በአንድ ላይ ሆነን ድምጽ እንድንሆንለት ይገባል እላለሁ።
2. እኔ የኢሮብ ህዝብ ድህነት እንዲቀረፍ፣ በአከባቢው የተለያዩ ለወጣቶቹ የስራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ ተቋማት እንዲመሰረቱ በሚደረገው ማንኛውም እንቅስቃሴ የፖሊቲካ አመለካከታችን ዕንቅፋት ሊሆነን ፈጽሞ አይገባም ነበር ብዬ አምናለሁ። አለመታደል ሆኖ ግን ዛሬ ከምንጊዜም በላይ ተከፋፍለናል። ስለዚህ እውነት የህዝብን ችግር ለመቀረፍ እንስራ ካልን፤ በኛ በኢሮቦች ደረጃ ልናደርጋቸው የሚንችላቸው የገንዘብና የሌላ ቁሳቁሶች እርዳታ በአንድ ላይ በአንድ መስመር በጋራ ልናደርግበት የሚያስችለን ከፖሊታካ ድርጅቶች ሆነ ከመንግስት ተጽዕኖ ነጻ የሆነ የራሳችን የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዲኖረን ያስፈልጋል ይገባልም።
3. ለኢሮብ ህዝብ ድህነት ተፈጥሮ የጣለብን ችግር ያለው አሉታ እንዳለ ሆኖ ሰው ሰራሽ ችግሮችም ተጨምረውበታል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ራሱ ህዝቡ ለእርሻ መሬት ሲል ደኑን በማወደም ያደረገው አሉታዊ አስተዋጽኦ እንዳለ ሆኖ፣ መንግስታትም መውሰድ የሚገባቸው ደኖችን የመንከባከብ እርምጃ በወቅቱ ባለመውሰዳቸው ለደኖቹ ብርሰት ከፍተኛ አሉታዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል ማለት ይቻላል። በተለይ ዴሞክራሲያዊ ነኝ የሚለው የኢህአዴግ መንግስት የኢሮብ ወረዳን ተፈጥሮአዊ ገጽታ ለመቀየር የወሰዳቸው እርምጃዎች ሆነ ለወጣቱ የስራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ ተቋማት በመገንባት በኩል የሰራው ስራ ኢምንት ነው ማለት ይቻላል።

   ስለሆነም ድህነቱ እንዲቀረፍ፣ በአከባቢው ለወጣቶቹ የስራ ዕድል ሊፈጥሩለት የሚችሉ ተቋማት እንዲመሰረቱ፣ አንድ ላይ ሆነን መንግሥትን መጠየቅ መቻል አለብን።ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ችሎታውና ዕውቀቱ ያላቸው ወገኖች በአከባቢው ለወጣቱ ስራ ሊፈጥሩ የምችሉ ተቋማት በማጥናት ጥናቱን ለመንግስትም ሆነ ለተለያዩ ኢንቨስት የማድረግ ችሎታ ላላቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ማቅረብ መቻል አለባቸው፣ አሁንም እውቀቱና ችሎታው ያላቸው ወገኖች ምድርቱ በከርሷ የያዘቻቸው ንጥረ ነገሮችን ማጥናትና ወደ ጥቅም ሊለወጡ የሚችሉበትን መንገድ ማፈላለግ መቻል አለባቸው።
4. ዛሬ በሀገራችን እየተሰራበት ያለው ህገመንግስት ዜጎች ህገመንግስቱን እስካልተጻረሩ ድረስ ጥቅማቸውን ለማስከበር በፈለጉበት መንገድ የመደራጀት መብትን ይፈቅዳል። ስለሆነም በሀገርቤት ያላችሁ ወገኖቻችን ህገመንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት መብታችሁን ለማስከበር፣ በህገመንግስቱ ጥላ ስር በመደረጃት ለመብታችሁ በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ መታገል መቻል አለባችሁ። በተለይ አሁን በኢሮብ ወረዳ ሰፍኖ ያለው ድህነትን በመቀነስ በአከባቢው ሠርቶ ለመኖር የሚያስችል ተስፋ እንዲፈነጥቅ

መንግስት ለአከባቢው መስጠት የሚገባውን ቱክረት እንዲሰጥ ለማድረግ እንዲቻል በአንድ በመቆም ለመብታችሁ ስትታገሉ ብቻ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል።

5. ዛሬ እኛ ኢሮቦች፣ የትናንቱ አባቶቻችን የነበራቸው ዓይነት ኢሮብነትና አንድነት አጥተናል፣ በመሆኑም ወጣቱ ትውልዳችን በኢሮብነቱ ላይ ተስፋ እየቆረጠ ነው። በአከባቢው በድህነትና በተለያየ ምክንያት ለመኖር ያልቻልን ቁጥራችን የማይናቅ ኢሮቦች ተሰደን በተለያዩ ሀገራት በስደተኝነት እየኖርን ነን። በትክክል ቁጥሩን ባላውቅም በተለይ በሰሜን አመሪካ፣ በሳዑዲ ዓረቢያና በእስራኤል ዛሬ በርከት ያለ ቁጥር ያለን የኢሮብ ተወላጆች እንደምንገኝ አውቃለሁ። ልክ እንደ ሀገርቤቶቹ እኛም በወጭ በስደት የምንኖር ኢሮቦች ተደራጅተን ለህዝባችን ችግር በጋራ ለመፍትሀ ሆነ ድህነቱን ለመቅረፍ በጋራ ለመስራት መቻል አለብን።

ስለሆነም እውነት ከልብ የወጣቶቻችን ስደት ለማስቀረት ከፈለግን በተለይ በውጩ ዓለም በስደት የምንገኝ የብሄረሰቡ አባላት አንድ ላይ በመቆም ድምጽ አልባ ለሆነው ህዝባችን ድምጽ ለመሆን መቻል አለብን። በተጨማሪም ማንኛውም የምንችለው እርዳታ በተናጠል በተለያየ ቡድን አማካይነት ከማድረግ በአንድ መስመር በአንድነት ለማድረግ መቻል አለብን። ይህን ለማድረግ ከልብ ከፈልግን ጠቃቅን ልዩነቶችን አስወግደን ሁላችንን የሚያቅፍ አንድ የእርዳታ ማህብር መስርተን በጋራ መንቀሳቀስ መቻል ይኖርብናል።

6. ዛሬ በኢትዮጵያ በትረ ስልጣኑን የጨበጠው የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት ዕድሜውን ለማራዘም ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ዋነኛው የከፋፍለህ ግዛ ዘዴ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነው። በመንግስት ሥልጣን ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ህወሓትም ይህን የከፋፍለህ ግዛ ዘዴውን በኛ በኢሮቦች መካከልም በሚገባ እየተጠቀመበት ነው። ህወሓት ዛሬ በመካከላችን የመንግስት ደጋፊና ተቃዋሚ በሚል ክፍፍል እንዲፈጠር አድርጓል፣ እርስ በርሳችን በጥላቻና በጥርጣሬ ዓይን እንድንተያይም ምክንያት እየሆነ ይገኛል። በመሆኑም ዛሬ ለህዝባችን ድህነት፣ለወጣቶቻችን ስደት መንስኤዎች ምን ናቸው በሚለው እኛ ኢሮቦች ስምምነት/አንድነት እንዳይኖረን በማድረግ ላይ ነው። ለምሳሌ ለወጣቶቻችን መሰደድ የመንግስቱ ደጋፊ ነን የሚሉ ወገኖች ለችግሩ እንደ መንስኤ ተቃዋሚዎችን ሲከሱ፣ መንግስቱን የሚቃወሙ ወገኖች ደግሞ በዋናነት መንግስትን ይከሳሉ። እንደኔው ዓይነት እስከዛሬ ከማንም ያልወገን ነን ባዮች ደግሞ እስከዛሬ ህዝባችን እየጠፋ እያየን እንዳላየን፣ እየሰማን እንዳልሰማን ከሁሉም ነገር ራሳችንን አግልለን የዳር ተመልካች ሆነን ማየትን መርጠን እንገኛለን። የህዝባችን ችግር እንዲቀረፍ፣ የወጣቶቻችን ስደት እንዲያበቃ ከልብ ከፈለግን በተለይ የኔው ዓይነት ትምህርት የቀመስን እስከዛሬ በዳር ተመልካችነት የቆምን ወገኖች ሳንውል ሳናድር አቋም ወስደን ለህዝባችን ደህንነት መታገል አለብን። በተለይ ተማርን የምንል ወገኖች ህዝብ እየተቸገረ፣ ወጣት ቀየውን ለቆ እየተበታተነ፣ ግማሹ በየባህሩ በየምድረበዳው ሙቶ እየቀረ መሆኑ እያየንና እየሰማን ጆሮ ዳባ ማለት መቆም መቻል አለበት። ይህ የወጣቶች ስደት እንዲቀር ማለት የሚገባን ሳንል፣ መጻፍ ያለበትን ሳንጽፍ፣ ማድረግ ያለብንን ሳናደርግ ብንቀር ነገ በታሪክ ተጠያቂ እንደምንሆን ማወቅ ይኖርብናል።

እንግዲህ በኔ በኩል ለህዝባችን ድህነት መቅረፍ፣ የወጣቶቻችን ስደት ለማሰቀረት ማድረግ አለብን የምላቸው የመፍትሂ ሃሳቦች ይህን ይመስላሉ።እናንተስ ምን ትላላችሁ?

በክፍል ሁለት *በስልጣን ላይ ባለው ገዢ ፓርቲ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ረገጣና ለገነዘብ ሲሉ ወጣቶችን ለስደት የሚመለምሉ ወንጀለኛ ግለሰቦች መኖርን* ለማሰቀረት ምን ማድረግ አለብን በሚለው የመፍትሂ ሃሳቦቼን/አስተያየቶቼን ይዤ እመለሳለሁ። የነገ ሰው ይበለን

ሱመ ነኝ ከምድረ ዓረብ